7ኛ ዓመት ቁጥር 9
7th Year No. 9

ባሕር ዳር መጋቢት 22/1994 ዓ/ም
Bahir Dar March 31st/2002

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

ዝክረ - ሕግ
ZIKRE-HIG

OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE IN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ	ISSUED UNDER THE AUSPICES OF THE COUNCIL OF THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE	ፖ.ማ.ቁ. 1324 ያንዱ ዋጋ ብር 2·50 Unit Price.....

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 65/1994 ዓ/ም

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት ማቋቋሚያና ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ

CONTENTS

PROCLAMATION No. 65/2002

Office of the Head of Government of the Amhara National Regional State Establishment and Determination of its powers and Duties Proclamation.

አዋጅ ቁጥር 65/1994 ዓ/ም

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የርዕሰ መስተዳድሩን ጽ/ቤት ለማቋቋምና ሥልጣንና ተግባሩን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

የአማራ ብሔራዊ ክልል ርዕሰ መስተዳድር በሕገ-መንግሥቱ የተጣለበትን ባለብዙ ፈርጅ ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት ይቻለው ዘንድ የራሱ ጽ/ቤት እንደሚኖረውና ይኸው ጽ/ቤት በብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱ ከፍተኛ የአስፈፃሚነት ሥልጣን የተሰጠው የክልል መስተዳድር ም/ቤቱ ጽ/ቤት በመሆን ጭምር የማገልገል ተጨማሪ ተልዕኮ እንደተሰጠው ተሻሽሎ በወጣው የክልሉ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 62 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ሥር አስቀድሞ የተደነገገ በመሆኑ ፤

PROCLAMATION No. 65/2002

A PROCLAMATION ENACTED TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT AND DETRMINATION OF POWERS AND DUTIES OF THE OFFICE OF THE HEAD OF GOVERNMENT IN THE AMHARA NATIONAL REGIONAL STATE.

Where as, it has been provided before hand under the provisions of sub-Arts, 1 and 2 of Art 62 of the revised National Regional Constitution that the Head of Government of the Amhara National Regional State shall have an office of his own so as to be able to efficiently discharge the multi Faceted constitutional responsibility bestowed upon him and that this same office would also be meant to serve, as an additional task, the purpose of an office of the council of the Regional government, a boby entrusted with the highest Executive powers of the National Regional State ;

ከዚህ በመነሣት የሕገ-መንግሥቱን ድንጋጌዎች ዋቢ አድርጎ ጽ/ቤቱን በሕግ መመሥረት፣ ተግባርና ኃላፊነቱን መወሰንና በተገቢው የሰው ኃይልም ሆነ ቁሳቁስ አደራጅቶ ሥራውን በተሟላ ሁኔታ ለማከናወንና ውጤታማ አስተዳደራዊ አገልግሎት ለማበርከት የሚችልበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የአማራ ብሄራዊ ክልል ምክር ቤት በ1994 ዓ.ም ተሻሽሎ በወጣው የክልሉ ሕገ- መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1/ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚከተለውን አዋጅ አውጥቷል።

ክፍል አንድ

ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ " የአማራ ብሄራዊ ክልል ርዕስ መስተዳድር ጽ/ቤት ማቋቋሚያና ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 65/1994 ዓ.ም "ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. " ርዕስ መስተዳድር" ማለት በ1994 ዓ.ም ተሻሽሎ በወጣው የአማራ ብሄራዊ ክልል ሕገ መንግሥት አንቀጽ 60 ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተመለከተው አካል ነው።

2. " የክልል መስተዳድር ምክር ቤት" ማለት በዚሁ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 57 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የተቋቋመው የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ

Where as, it has, having this in mind, been of necessity to Legally establish the office, determine its duties and responsibilities and thereby create favorable conditions with reference to the provisions of the constitution, whereby it would manage to organize itself with appropriate manpower and material resources with the view to carrying out its business to the maximum possible and render an effective administrative service thereof;

Now, therefore, the council of the Amhara National Regional State, pursuant to the powers vested in it, under Art, 49 sub-arts, 3/1 of the revised National Regional Constitution, hereby proclaims as follows.

PART ONE

GENERAL

1. Short Title

This proclamation may be cited as " The Amhara National Regional State Head of Government Office Establishment and determination of Powers and responsibilities proclamation No 65/2002".

2. Definitions

Unless the context requires otherwise, in this proclamation: -

1. " Head of Government " is the organ referred to under Art, 60 sub –art, 1 of the 2001 revised constitution of the Amhara National Regional State.

2. " Council of the Regional government" is the highest Executive organ of the Amhara National Regional State established pursuant to the provisions of

መንግሥት ከፍተኛ የሕግ አስፈፃሚ አካል ነው፡

3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤትና እንደአስፈላጊነቱ በብሔረሰብ አስተዳደር፣በወረዳ አስተዳደርና በቀበሌ አስተዳደር እንዲሁም የክልል መስተዳድሩን ወክለው ይሠሩ ዘንድ በተመረጡ ሥፍራዎች በተቋቋሙ ወይም በሚቋቋሙ የአስተዳድር ጽ/ቤቶች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

ክፍል ሁለት

ስለ ርዕሰ መስተዳድሩ ጽ/ቤት መቋቋም፣ አላማ፣ አደረጃጀት፣ ሥልጣንና አመራር

4. ስለ ርዕሰ መስተዳድሩ ጽ/ቤት መቋቋምና ተጠሪነት

1. የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት ከዚህ በኋላ "ጽህፈት ቤቱ" እየተባለ የሚጠራ ራሱን የቻለና ሕጋዊ ሰውነት ያለው መንግሥታዊ አስፈፀሚ መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

2. የጽ/ቤቱ ተጠሪነት በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 63 ንዑስ አንቀጽ 2 በተደነገገው መሠረት ለርዕሰ መስተዳድሩና ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ነው፡፡

5. ዓላማ

የጽ/ቤቱ ዓላማ የብሄራዊ ክልላዊ መንግሥቱ ከፍተኛ አስፈፃሚ አካል የተጣለበትን ሕገ- መንግሥታዊ ኃላፊነት በብቃት እንዲወጣ ሁለንተናዊ የአሰት ከአሰት ድጋፍ ማበርከትና ተልዕኮውን በተቀነባበረና ስልታዊ በሆነ አሠራር በመደገፍ ማሟላት ነው፡፡

Art, 57 sub –art –1 of this constitution.

3. Scope of Application

This proclamation shall apply to the office of the Regional head of Government and the Administrative Offices established or to be established within the Nationality Zone, Woreda and Kebele Administrations as well as those selected areas of operation representing and acting on behalf of the regional government, as may be necessary

PART TWO

Establishment, Objective, Organization, Powers and Leadership of the Office of the Head of Government

4. Establishment and Accountability of The Office of the Head of Government

1. The office of the Head of Government of the Amhara National Regional state (Hereinafter) referred to as "the Office" is hereby established by this proclamation as a governmental executive organ being an entity with its own autonomy and legal personality.

2. The accountability of the office is both to the head and the council of the regional Government as provided for under Art, 63 sub-art, 2 of the constitution.

5. Objective

The objective of the office is to render an all-out day-to-day support enabeling the highest Executive organ of the National Regional State to efficiently discharge its constitutional responsibility as well as make it successful by upholding its mission in a systematized and strategic exercise and manner thereof.

6. ስለ ሌሎች የተዋረድ አስተዳደር ጽ/ቤቶች ምሥረታና አደረጃጀት

1. በብሔራዊ ክልሉ ውስጥ በሚገኙ የብሔረሰብ ዞኖች፣ ወረዳዎችና ቀበሌዎች ተመሳሳይ ተልዕኮ ያላቸው የተዋረድ አስተዳደር ጽ/ቤቶች በዚህ አዋጅ መሠረት ሕጋዊ ሰውነት አግኝተው ተቋቁመዋል::

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ሥር የተመለከቱት የየደረጃው አስተዳደር ጽ/ቤቶች ሕገ-መንግሥቱን መሠረት አድርገው በትይዩ ለተደራጁት ወይም ለሚደራጁት የአስተዳደር ም/ቤቶች ጭምር ጽ/ቤቶች ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ::

3. ጽ/ቤቶቹ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ሥር ለብሔራዊ ክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ጽ/ቤት የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር ለሥራቸው ባስፈለገ መጠን ተግባራዊ የማድረግ መብትና ግዴታ ይኖራቸዋል::

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ሥር የሠፈሩት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የብሔራዊ ክልላዊ መንግሥቱ ርዕሰ መስተዳድር በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 60 ንዑስ አንቀጽ 3 ፊደል ተራ ቁጥር ሸ ሥር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ከብሔረሰብ ዞኖችና ከባሕር ዳር ልዩ ዞን ውጭ በተመረጡ አካባቢዎች በክልልና በወረዳ መካከል ሌሎች የአስተዳደር ጽ/ቤቶችን ሊያቋቁሙና ተጠሪዎቻቸውን ሊሰይም ይችላል:: ዝርዝሩ የክልል መስተዳድር ም/ቤቱ በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል::

6. Establishment and Organization of other subordinate offices of Administration

1. There are hereby established other offices of administrations at all levels of Nationality Zones, woredas and Kebeles across the National Regional state which shall have been conferred with the like mission having acquired legal personality pursuant to this proclamation.

2. The hierarchical Administrative Offices cited under sub-article 1 of this Article hereof may also serve as the offices for parallel Administrative councils organized or to be organized in accordance with to the Constitution.

3. The offices shall have the rights and obligations to exercise those duties and responsibilities vested in the office of head of the National Regional Government as provided for under Art, 8 of this proclamation hereunder, to the extent required for the performance of there respective deeds.

4. Without prejudice to the provisions stipulated under sub-arts. 1 and 2 of this article hereof, the Head of Government of the National Regional state may, pursuant to the powers vested in him, by virtue of Art, 60 sub-art,3/H/ of the constitution, establish other administrative offices and thereby designate their respective agents, as between the region and the Woredas in those selected places outside the nationality Zones as well as the Bahr dar special Zone. Particulars shall be determined in a regulation to be issued by the council of the Regional government .

7. ድርጅታዊ አቋም

ጽ/ቤቱ ርዕሰ መስተዳድሩንና ምክትል ርዕሰ መስተዳድሩን በሙያ አገልግሎት የሚያግዙ አማካሪ ተሿሚዎችን ጭምር የያዘ ሲሆን ይህንኑ በማካተት አላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስፈልገውን ድርጅታዊ መዋቅር አጥንቶ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት በማቅረብ ያስወስናል።

8. የጽሕፈት ቤቱ ሥልጣንና ተግባር

ጽሕፈት ቤቱ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚከተሉት ዝርዝር ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. ለርዕሰ መስተዳድሩና ለክልል መስተዳድር ምክር ቤቱ አጠቃላይ አስተዳደራዊ ግልጋሎት ይሰጣል፤ ለዚህም የሚያስፈልገው የሰው ኃይልና ቁሳቁስ ተሟልቶና ተደራጅቶ መገኘቱን ያረጋግጣል፤

2. ዝርዝሩ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው መመሪያ የሚወሰን ሆኖ ለርዕሰ መስተዳድሩ፤ ለምክትል ርዕሰ መስተዳድሩና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው ከፍተኛ የክልሉ መንግሥት ባለሥልጣናት ተገቢውን የፕሮቶኮል ሽፋን ይሰጣል፤

3. ለክልል መስተዳድር ምክር ቤት አባላት መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች የሚያስፈልጉትን የመሰብሰቢያ ቦታዎች ያመናዳል፣ የሥራ ማቀላጠፊያ መሣሪያዎችና ሌሎች ተዛማጅ ቁሳቁሶችን ያቀርባል፣ ለተሰብሳቢዎች ተገቢው የመስተንግዶ አገልግሎት ተሟልቶ መቅረቡን ይከታተላል፤

4. የክልል መስተዳድሩ ምክር ቤት ቃለ-ጉባዔዎችና ሌሎች ሠነዶች

7. Organizational Status

The office shall, while being an entity as to include advisor-appointees with the view to assisting with professional service both the Head and Deputy Head of Government, study and submit an organizational structure necessary to accomplish its objective to the council of the regional Government for decision thereof.

8. Powers and Duties of the Office

The office shall, in accordance with this proclamation, have the following specific powers and duties; -

1. Provide general administrative service to the Head and the council of the Regional Government and thereby ensure that all the necessary human and material resources are availed in a rather fullfiled and organized manner for the cause;

2. With details to be outlined in a specific directive to be issued pursuant to this proclamation, render appropriate protocol coverage to the Head of Government, Deputy Head of Government as well as those high-ranking regional state officials concerned;

3. Prepare meeting places necessary for the holding of ordinary and extraordinary sessions of the members of the council of the regional Government, provide facilitative devices and other related items as well as follow up that proper services of good hospitality are fully delivered to those participating in the said meetings;

4. Prepare a confidential duty room, where-in the minutes and other documents of

በአግባቡ ተፈርመው ፣ ትክክለኛነታቸው ተረጋግጦና በአይነት እየተለዩ ተመዝግበው በሚገባ የሚያዙበትንና ደህንነታቸው ተጠብቆ የሚቀመጡበትን ምስጢራዊ የሥራ ክፍል ያሰናዳል፣ ያደራጃል፣ ብቃት ያለው የሰው ኃይል መመደቡን ያረጋግጣል፣ አስተማማኝ የቁጥጥር ሥርዓት ይዘረጋል፤

the Council of the Regional Government may be kept with proper care and safety after having been signed, verified, identified in kind and duly registered, organize and furnish same, ensure that it is provided with an efficient staff and put in place a reliable control system;

5. በክልል መስተዳድር ምክር ቤቱ የሚወጡ ደንቦች በወቅቱ ወደ እንግሊዝኛ ቋንቋ ተተርጉመው በክልሉ ዝክረ ሕግ-ጋዜጣ የሚታተሙበትንና ለሚመለከታቸው የመንግሥት አካላትም ሆነ ለተገልጋዩ ሕብረተሰብ ውጤታማና ቀልጣፋ በሆነ ዘዴ መሠራጨታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

5. Follow up and supervise that the regulations issued by the council of the Regional Government are translated into English on time, publish on the Ziker Hig Gazette of the regional state and officially distribute to those concerned Governmental bodies and the public at large seeking for the service in an effective and expedient method thereof;

6. የክልል መስተዳድር ምክር ቤቱ የሚያወጣቸውን መጽሔቶች፣ ጋዜጦችና በራሪ ጽሁፎች ዝግጅት፣ ሕትመትና ሥርጭት ሥራ በበላይነት ይመራል፣ ይከታተላል፤

6. Oversee and follow up the activities of preparation, publication and distribution of magazines, newspapers and pamphlets issued by the Council of the Regional Government;

7. የክልል መስተዳድር ምክር ቤቱ ህትመትና አዲዮቪዥዋል መረጃ አገልግሎት መስጫ ክፍል በዘመናዊ ዘዴ እንዲደራጅና እንዲጠናከር ያደርጋል ፣ የመስተዳድር ምክር ቤቱ ቃል አቀባይ በመሆን ይሠራል፣ ለክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት አባላት፣ በርዕሰ መስተዳድሩ ጽ/ቤት ለሚገኙ አማካሪዎችና ደጋፊ ኤክስፐርቶች የቤተ-መጽሐፍት፣ የምርምርና የመረጃ አገልግሎት ያበረክታል፤

7. Organize and strengthen the publication and audio-visual information service delivery division of the council of the regional government in a modern way, serve in a capacity of a spokes- person to the Governmental Council as well as provide library, research and information service to the members of the council of the Regional Government, advisors and supporting experts staffing the office of the Head of Government;

8. ዝርዝሩ ይህንን ደንብ ለማስፈፀም በሚወጣ መመሪያ የሚወሰን ሆኖ ከሃገር ውስጥና ከውጭ አገር ለሚመጡ የክልሉ እንግዶች በመስተዳድር ምክር ቤቱ ስም ሁለገብ የመስተንግዶ አገልግሎት ይሰጣል፣ ለዚህም የሚያስፈልገውን ድርጅታዊ ብቃትና ዝግጁነት በየጊዜው ያሳድጋል፤

9. የብሄራዊ ክልላዊ መንግሥቱን አስፈፃሚ አካላት እንደገና ለማደራጀትና ሥልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 60/1994 ዓ.ም አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 4 እና በሌሎች ሕጎች በተደነገገው መሠረት ለርዕሰ መስተዳድሩ ጽ/ቤት ተጠሪ የሆኑ አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶችንና ድርጅቶችን ለይቶ ይመዘግባል፣ ከርዕሰ መስተዳድሩ ጋር የሚኖራቸውን የሥራ ግንኙነት በማቀላጠፍ ያግዛል፤

10. በመደበኛና በካፒታል በጀት ሊሚያከናውናቸው የሥራ ፕሮግራሞች የሚያስፈልገውን አመታዊ የማስፈፀሚያ በጀት ረቂቅ ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

11. የጽ/ቤቱ መደበኛ እቅዶችና ክልላዊ ባህሪይ ያላቸው ሥራዎች ተጣጥመው ተግባራዊ የሚሆኑበትን የአሠራር ስልት ይቀይሳል፣ በመስተዳድር ምክር ቤቱ ስም የሚጠሩ ክልላዊ አወደ ጥናቶች፣ ሲምፖዚየሞች፣ ኮንፈረንሶችና ሌሎች ስብሰባዎች በተቀመጠላቸው የጊዜ ሠሌዳ መሠረት እንዲከናወኑና እንዲፈፀሙ ያደርጋል፤

8. With details to be specified in a directive to be issued for the implementation of this proclamation afterwards, welcome and provide an all-out service of hospitality, in the name and on behalf of the Regional Government, to those guests of the regional state from home and abroad and further enhance its organizational capacity and preparedness necessary for such an undertaking from time to time;

9. Pursuant to the provisions of Art, 5 sub-art, 4 of the National Region state Executive Organs' Re-organization and Determination of Powers and Duties Proclamation No 60/2001 and other Laws, identify and duly register those executive offices and enterprises made accountable to the office of the Head of Government and assist in the process of facilitating and expediting their working relationships with the Head of Government;

10. Prepare the annual executionary budget proposal necessary to carry out its normal work programs designed to be undertaken both by recurrent and capital budget and implement same upon approval;

11. Devise working strategies and mechanisms in which regular plans of the office and those tasks of regional character may be excuted in full compatibility with one another and strive for the smooth undertaking and timely completion of regionwide work-shops, symposia, conferences and other meetings called upon in the name and on behalf of the Governmental Council;

12. አስተዳደራዊ ፍትህ ጠይቆ ወደ ርዕሰ መስተዳድሩ ጽ/ቤት የሚመጣ ማናቸውም ባለጉዳይ ያለአንዳች ውጣ ውረድና እንግልት ቅሬታውን ለማስማት ይቻለው ዘንድ አግባብ ካለው የሥራ ኃላፊ ወይም ባለሥልጣን ጋር በወቅቱ የሚገናኝበትን አመቺ የአሠራር ስልት ቀይሶ በሥራ ላይ ያውላል፤

12. Devise and implement an expedient working mechanism to assist any party coming to the office of the Head of Government and having brought about any form of petition seeking for a possible administrative justice so that he would be able to have a prompt access to the relevant official or department head thereof and have his grievance entertained without an Impediment or any sort of inconvenience whatsoever;

13. በሥሩ የተዋቀረ አደረጃጀቶች ቀልጣፋና ጥራቱን የቀጠበ መንግሥታዊ አገልግሎት መስጠታቸውን ይከታተላል፣ ጉድለት መፈፀሙን ሲረዳ አፋጠኝ የእርምትና የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤

13. Follow up that its subordinate hierarchical structures and setups deliver speedy and qualitative Governmental service and thereby take corrective and rectifying measures, should it find or be aware of any possible defect in that respect;

14. የበታች አስተዳደር ጽ/ቤቶችን በሰው ኃይል ሥልጠናና በቁሳቁስ አቅርቦት ረገድ እንደአስፈላጊነቱ ይደግፋል፣ ያጠናክራል፣ ብቃት ባለውና የስነ-ምግባር ደረጃውን በጠበቀ የሰው ኃይል መገልገላቸውን ይከታተላል፣ ያግዛል፤

14. Support and strengthen the lower-level offices of administrations with man-power training and provision of material supplies, as may be necessary, follow up and assist their effort to utilize an efficient and ethically-elevated staff;

15. ለተዋረድ አስተዳደር ጽ/ቤቶች በየጊዜው የሚመደበው የአይነትም ሆነ የጥሬ ገንዘብ ሃብት ውጤታማ በሆነ መንገድ በሥራ ላይ የዋለ ስለመሆኑ የሚያረጋግጥ አስተማማኝ የቁጥጥር ሥርዓት የተበጀተለት መሆኑን ይከታተላል፣ ለዚህም ስኪታማነት የውስጥ አዲት አገልግሎቶች እንዲጠናከሩ ያደርጋል፤

15. Follow up that there exists a reliable system of control with the view to ensuring that whatever material and Financial resources which might from time to time, be allocated to the hierarchically-lower offices of administrations is properly and effectively utilized and thereby strengthen internal Audit services to that end.

16. በየደረጃው ባሉ የአስተዳደር ጽ/ቤቶች ዘንድ እቅድ የማውጣት፣ ተግባራዊ የማድረግና አፈፃፀሙን የመገምገም ባህል በሠራተኛው ተሣትፎ እንዲጐለበት ያላሰለሰ ጥረት ያደርጋል፤

16. Strive hard without any reservation towards the promotion and enhancement of a culture of an exercise with plan formulation, implementation and evaluation of activities with possible participation of employees on the part of those offices of administrations at various levels;

17. ለርዕሰ መስተዳድሩ የሚቀርቡ አስተዳደራዊ አቤቱታዎችን ዓይነት፣ ብዛትና መንስኤ በየጊዜው እያጠና የሕዝብ አቤቱታዎች በየደረጃው ባሉ የክልሉ መንግሥት አስተዳደር አካላት መፍትሄ የሚያገኙበትን መንገድ በመጠቆም ለውሣኔ ሰጭ አካላት ያቀርባል፤

17. Study, on regular basis the cause, category and amount of administrative petitions brought about to the attention of the Head of Government from time to time and propose possible means and ways, through which to obtain remedies for public grievances at the level of pertinent Government Administrative bodies of the Regional State, to be ultimately submitted to the decision-making organs thereof;

18. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሣል፣ ይከሠሣል፤

18. Own property, enter into contracts and sue or be sued in its own name;

19. ርዕሰ መስተዳድሩ ለሥራው መሣካት ባስፈለገው መጠን የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

19. Carryout such other tasks assigned to it as may be necessary for the accomplishment of the functions bestowed upon the Head of Government.

9. ስለ ጽሕፈት ቤቱ አመራርና ተጠሪነት

9. Leadership and Accountability of The Office

1. ጽሕፈት ቤቱ በርዕሰ መስተዳድሩ በሚሾም አንድ የበላይ ኃላፊ ይመራል፤

1. The office shall be headed by a superintendent, whom the head of Government appoints;

2. የጽ/ቤቱ ኃላፊ ተጠሪነቱ ለርዕሰ መስተዳድሩ ነው::

10. የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ሥልጣንና ተግባር

1. የጽ/ቤቱ ኃላፊ ከርዕሰ መስተዳድሩ በሚሰጠው አመራር መሠረት የጽሕፈት ቤቱን ሥራዎች በበላይነት ይመራል፣ ጽ/ቤቱን ያስተዳድራል::

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የጽ/ቤቱ ኃላፊ:-

ሀ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ሥር የተመለከቱትን የጽ/ቤቱን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፣

ለ. የጽ/ቤቱን ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች በሃገሪቱ የሲቪል ሠርቪስ ሕግ መሠረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣

ሐ. የጽ/ቤቱን አመታዊ በጀትና የሥራ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ለርዕሰ መስተዳድሩ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣

መ. ለጽ/ቤቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጭ ያደርጋል፣

ሠ. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ስር ለጽ/ቤቱ በተሰጠው የስልጣን

2. The Head of the office is accountable to the Head of Government.

10. Powers and Duties of the Head of the Office

1. The Head of the Office shall, on the basis of the guidance handed down to him by the Head of Government, direct over the activities of the office and administer thereto.

2. Without prejudice to the provisions of sub-art 1 of this article hereof the head of the office shall; -

a). Put in effect the powers and duties of the office as provided for under Art,-8 of this proclamation hereof;

b). Employ and Administer the support staff of the office in accordance with the country's civil service laws;

c). Prepare and submit the annual work program and budget proposal of the office to the Head of Government and implement accordingly upon approval thereof;

d). Disburse money and authorize expenditures in accordance with the approved work program and budget appropriation;

e). Represent the office in its dealings with 3rd parties having

ክልል ተወስኖ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ጽ/ቤቱን ይወክላል፤

ረ. የጽ/ቤቱን የሥራ እንቅስቃሴና የሂሣብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለርዕሰ መስተዳድሩ ያቀርባል፤

ሰ. በርዕሰ መስተዳድሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል::

3. የጽ/ቤቱ ኃላፊ ለጽ/ቤቱ የሥራ ቅልጥፍና ባሰፈለገ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለጽ/ቤቱ የበታች ሥራ ኃላፊዎችና ሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል ::

ክፍል ሦስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

11. የጽ/ቤቱ በጀት

የጽሕፈት ቤቱ በጀት በክልሉ መንግሥት የሚመደብ ይሆናል::

12. የሂሣብ መዛግብት

1. ጽሕፈት ቤቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል::

2. የክልሉ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በሕግ የተሰጠው መብትና ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የጽ/ቤቱ የሂሣብ መዛግብትና ሌሎች ገንዘብ ነክ ሠነዶች በክልሉ ዋና አዲተር መሥሪያ ቤት በየጊዜው ይመረመራሉ::

recourse to and been limited with its powers as defined under Art, 8 of this proclamation hereof;

f). Prepare the activity and Financial report of the Office and submit same to the Head of Government;

g). Perform such other duties as may be referred to him by the Head of Government.

3. The Head of the office may delegate part of his powers and duties to the subordinate officials and other employees in as much as such delegation has been required for the accomplishment of the task of the office thereto.

PART THREE

MISCELLANEOUS PROVSIONS

11. Budget of the Office

The budget of the office shall be allocated by the regional state.

12. Books of Account

1. The office shall maintain complete and accurate books of account.

2. Without prejudice to the rights and powers vested in the Regional Finance and Economic Development Bureau as provided by law, the books of account and other Financial documents shall be examined by the Auditor General of the Regional State on periodic occasions.

13. የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጐች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ ውስጥ የተሸፈኑትን ጉዳዮች በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም::

13. Repealed and Inapplicable Laws

Any law, regulation, directive or customary practice inconsistent with this proclamation shall not apply with respect to matters provided for therein.

14. ደንቦችና መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን

1. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን ደንቦች ሊያወጣ ይችላል::

2. የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ይህንን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉትን ልዩ ልዩ መመሪያዎች ሊያወጣ ይችላል::

14. Power to Issue Regulations And Directives

1. The council of the Regional Government may issue Regulations necessary for the execution of this proclamation.

2. The Head of the Regional Government may issue various directives necessary for the implementation of this proclamation and Regulations issued thereunder.

15. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ታይቶ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

ባህር ዳር

መጋቢት 22/ቀን 1994 ዓ.ም

ዮሴፍ ረታ

የአማራ ብሄራዊ ክልል

ፕሬዚዳንት

15. Effective Date

This proclamation shall enter into force as of the date of its consideration and approval by the Regional Council.

Done at Bahir dar

This 31st day of March 2001

Yosef Retta

President of the Amhara

National Regional State

7ኛ ዓመት ቁጥር 10
7th Year No. 10

ባህር ዳር መጋቢት 22/1994 ዓ/ም
Bahir Dar 31st Day of March, 2002

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

ዝክረ ህግ

ZIKRE HIG

Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

1324
ያንዱ ዋጋ ብር 4.60
Unit price ---------

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 66/1994 ዓ/ም
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፖሊስ አደረጃጀትና አስተዳደር መወሰኛ አዋጅ

Contents

Proclamation No. 66/2002
A Proclamation to Provide for the Organization of the Amhara National Regional State Police Force

አዋጅ ቁጥር 66/1994 ዓ/ም

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ፖሊስ አደረጃጀትንና አስተዳደርን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

ለአማራ ብሔራዊ ክልል እና ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስታት ታማኝነት ያለው እና በሕገ-መንግስቱ መሠረት ለሚወጡ ሕጐች ተገዢ የሆነ፣ ለሙያው ተገቢ ሥልጠና የተሰጠውና ብቃት ያለው፣ ለህዝብ አገልጋይና ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን የሚያከብር፣ ለተያያዝነው ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ አስተዋጽኦ የሚያደርግና የህዝብን ሠላምና ደህንነት የሚጠብቅ የተጠናከረ ሲቪል የፖሊስ ተቋም እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ተሻሽሎ በወጣው የብሔራዊ ክልሉ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/9/እና 1 ድንጋጌዎች ስር በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሚከተለውን አዋጅ አውጥቷል።

Proclamation No. 66/2002

The Organization and Administration of the Amhara National Regional State Police Force Proclamation

WHEREAS, it has become necessary to have a strong civil police institution which is loyal to the constitution of the Amhara National Region and the Federal Democratic Republic of Ethiopia and governed by laws enacted in accordance with the constitution that has the adequate training and efficiency in the police Profession, that serves and ensures Peace and Security of the Public, contributes to the ongoing democratic System building efforts and duly respects human and democratic rights and freedoms;

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara National Region, in accordance with the powers vested in it under Article 49 Sub-articles 3/9 and 1 of the Revised Constitution of the Region, hereby Proclaims as follows: